M06/1/A1AMH/SP1/AMH/TZ0/XX

22060015

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 1**

Monday 22 May 2006 (morning)
Lundi 22 mai 2006 (matin)
Lunes 22 de mayo de 2006 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only. It is not compulsory for you to respond directly to the guiding questions provided. However, you may use them if you wish.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages. Le commentaire ne doit pas nécessairement répondre aux questions d'orientation fournies. Vous pouvez toutefois les utiliser si vous le désirez.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento. No es obligatorio responder directamente a las preguntas que se ofrecen a modo de guía. Sin embargo, puede usarlas si lo desea.

**ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ (መርጠሽ) አስተያየት ስጥ(ስጭ)።**

**1. (ሀ)**

**እብስ/ አለ**

*የጥቁር ዘብ - ምርኩዝ በሩ፣*
*በስም ዕዳ - ክብር አዳሩ፣*
*ወንዝ ሽጡን - እንደርድሮ፣*
*በየተራ - አስገብሮ፣*
*በደን ጫካ - ዱር ተከቦ፣*
*ቀለም ዳምኖ - ምድር አስዉቦ፣*
*ዙር መቀነት - አከናንቦ፣*
*ካለት አለት - ተፈጥርቆ፣*
*ያገር መኩሪያ - ጥሪት ነጥቆ፣*
*እብስ አለ - ሄደ ርቆ።*
*ያባይ ውሐ - አልማዝ ወርቁ፣*
*ጥቅም አልቦ - ብርቅ ድንቁ።*
*ዛፍ ጉማጁን - አተራምሶ፣*
*ገጸ ምድሩን - ልሶ ልሶ፣*
*ሰዉ አራቁቶ - ባዳ አሳብሶ፣*
*ምድረ አበሻን - አስለቅሶ፣*
*ጥርግ አለ - ሆድ አስብሶ።*
*ወዶም ባይሆን - ተቸግሮ፣*
*ካንዱ ገሮ - ሌላ'ሽሮ፣*
*ካፋፍ ገደል - ተገማሽሮ፣*
*ግንድ ጉቶ - አገላብጦ፣*
*ያገኘዉን - ተፍቶ ዉጦ፣*
*ግዮን ሽፍታው - ሀብት አሚጦ፣*
*ላይመለስ ሄደ - አግምጦ።*
*ካናት ሜዳ - ተጠቅሎ፣*
*ገደሏ ሥር - ተሸብሎ፣*

*ቤት ለ’ምቦሳ - ለምለም አቅፎ፣*
*ኖር ባይለዉ - አነጣጥፎ፣*
*ካገሩ ልጅ - ተኮራርፎ፣*
*ከዳር ድንበር - አልፎ ተርፎ፣*
*ባፈር ቀልቶ - እየደማ፣*
*ዓባይ ልጁን - እያስጠማ፣*
*ዋቶ አደረ - ሰዉ ከተማ።*
*ቁጭት አዝሎ - እምባ አቅዞ*
*እብስ/ አለ - ግቱን ይዞ።*

ውድአላት ገዳሙ፣ <u>እናትና ልጅ</u>፣ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት፣ **1996**።

– በግጥሙ ውስጥ አባይ ወንዝ እንደምን ቀርብዋል?

– ገጣሚዋ በአንባቢው አመለካከት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የተጠቀመችባቸው ቴክኒኮች ላይ አስተያየት ስጥ።

– የግጥሙን ዋና ጭብጥ ለመረዳት ያገዙህ ነጥቦች የትኞቹ ናቸው?

– ስለግጥሙ ያለህ አጠቃላይ አስተያየት ምንድነው?

**1.** (ሰ)

ዛሬ ምንድን ነካው እንዲህ ዐይን አፍጦ ፥
ሰው ጥሎ የጠፋ ከሰው ጋር ተቀምጦ ።
... እንዲያው ትዝታዬ . . . ’

ማንጠግቦሽ ፥ በዚያ በሚያምር ድምጿ ከየሰዉ ግን ባር ላይ የምታነብ ይመስል ፥ እንዳሰኛት በሚመጣላት ግጥም ዜማዋን ስታንቆረቁር መቆየቷን ቡና ቤቱ ጎራ ካልኩበት ጊዜ ጀምሮ ባውቅም ፥ እኔ አጠገብ ደርሳ ፊት ለፊቴ ቆማ ለኔ መዝፈንዋን ግን አላጤንኩትም ነበር ።

“ ...ዛሬ ምንድን ነካው እንዲህ ዐይን አፍጦ ፥
ሰው ጥሎ የጠፋ ከሰው ጋር ተቀምጦ . . . ” የሚሉት ስንኞች ግን የጆሮዬን ታምቡር ሲደውሉት ፥ መልዕክቷ ከሕሊናየ ዘልቆ ኖሮ መለስ ብዬ አየኋት ። መሰለች ‘ ድገሚው ’ ስትላትና ‘ ጸጉ አንተን እኮ ነው ’ ብላ አጠገቤ ስትቀመጥ ፥ እኔም ከተጓዝኩበት የሐሳብ ዓለም ተሽቀንጥሬ ስመለስ እኩል ሆነ ።

“ ምን አለች ? ” አልኩና ተቀድቶ እፊቴ የቆየውን መጠጥ ባንድ ትንፋሽ ጨለጥኩት ።

ማንጠግቦሽን በዚህ ሞያዋ ሳውቃት ጥቂት ወራት አልፈውኛል ። የድምጿ ቅላጼና የምታወርደው ግጥም ዘወትር ይማርከኛል ። ያን መጠጥ ቤትም ማዘውተር የጀመርኩት ለርሷ ስል ነበር ። መጀመሪያ ካየኋት ቀን አንሥቶ በተመለከትኳት ቁጥር ዱሮ እንደማውቃት ሁሉ ልቤ ይሸበራል ። በሕይወት የተፈራረቀባት የኑሮ ውጣና ውረድ በመልኳ ላይ ምልክቱን በመተዉ ትንሽ ግር ቢያሰኝም ፥ አትኩሮ ለተመለከታት ዕድሜዋ በኻያዎቹ አጋማሽ ላይ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም ። ግንባረ ሰፊ ነች ። በስሜት ተመስጣ ስታዜም እንደ፣ ቋጠር ፥ እንደ፣ ፊታ የሚለው ፊቷ መሥመር ቢያበጅም ፥ በዝምታ ስትቀመጥ ግን ቆዳዋ አያሽበሽብም ። ዐይኖቿ ጎላ ያሉ ናቸው ፥ ጉድ ለማየት ያፈጠጡ የሚመስሉ ። አፍንጫዋ አነስ ብሎ በቀጥታ ይወርድና ጫፉ ወደ ላይ ቀና ያለ ነው ። ስስ ከናፍሯ እንደሚያስተጋባው ድምጿ አይሰፋም ። አፏ ትናንሽ ነጫጭ የፊት ጥርሶቿን ለማሳየት ያህል ብቻ በመጠኑ ተከፍቶ የሚወጣው ድምፅ ግን መጠኑን ያለፈ ነው ። በዝያ ቅላቷ ላይ ከአንደኛው ጆሮ ግንዷ እስከ ሌላው ድረስ አገጯን አካሎ በሁለት ድርብ የተሠመረው ንቅሳቷ ከርቀት ይታያል ። እጆቿን ቀጭን ወገቧ ላይ አሳርፋ ከዜማዋ ጋር በዝግታ የምትነቀንቃቸውን ትከሻዎቿን እያጀቡ ጡቶቿ ሲንቀጠቀጡ ወርደው የሚፈርጡ ይመስላሉ ። የመሰለችን ጥያቄ በመቀበል ግጥሙን በድጋሚ አንቆረቆረችው ፥ በባለ መሰንቆ እየታጀበች ። “ ግን ግጥም እንዴት ይመጣላታል ? ” አለች መሰለች ፥ በአድናቆት እየተመለከተቻት ። እኔንም የሚደንቀኝ ይኸው ነው ። እርግጥ ብዙ አዝማሪዎች ግጥም የማፍለቅ ችሎታ ቢኖራቸውም ፥ ከሁለትና ከአራት ስንኝ በላይ ማውረድ አይችሉም ። ማንጠግቦሽ ግን በአንድ ሐሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዐሥርና ከዚያም በላይ ስንኝ ያሏቸው ግጥሞችን የማፍለቅ ተሰጥኦዋ ዘወትር የሚገርመኝ ነው ።

ከፍ ፣ ዝቅ ፣ ረዘም ፣ አጠር እያለ እንዳሻት በሚሰባበር ድምጿ ዜማዋን ቀጠለች ፣ ትናንሽ ነጫጭ ጥርሶቿን እያሳየች ።

“ እንዲያው ትዝታዬ . . . እንዲያው ትዝታዬ
ዱሮና ካቻምና ፣ አምና ትላንትና
ያለፈ የሆነ ‘ ትዝታ ’ ነውና
ይኸም ጥሎህ ሒዶ ትዝታህ ከሚሆን
የዛሬን ዛሬ አርገው ፣ ተጫወት አብረኸን . . . ”

ባዛዜሟ ከልክ ያለፈ ተደሰትኩ ። ግጥሟ ውስጤን ዘልቆ ተሰማኝ ። መለስ ብዬ ፣

“ ጎሽ እስኪ ሁለቱንም ቢራ ጋብዢልኝ ” አልኳት መሰለችን ።

“ ይልቅ ብሩን ብትለጥፍላቸው አይሻልም ? ” አለችኝ ።

“ አ ! ሴትዮ እሱን የምወስነው እኔ ራሴ ነኝ ። ሁለት ቢራ ስጪቸው ። ”

ትዕዛዝ ሰጠሁ ። ቢራውን በምስጋና ተቀበሉና ወደ ሌላ ባለተራ ፊታቸውን መለሱ ።

ዐይኖቼ ተከትለዋት ሔዱ ። በሕይወቴ ከማውቃቸው ሴቶች መኻል ሌላ ማንጠግቦሽን አገኘ ይመስል በሐሳብ የኋሊት ነጐድሁ ። የሚሰማኝን ስሜት ማጋራት የምችል መስሎኝ ፣ ‘ አንድ ፍሬ ልጅ ናትኮ ! አታሳዝንሽም ? ’ አልኳት መሰለችን ።

“ ምን ታሳዝናለች ፣ ደስ ታሰኛለች እንጂ ! ”

“ እኮ ደስ ስለምታሰኝ አታሳዝንሽም ? አንድ ፍሬ ልጅ ናትኮ ! ” አልኳት እንደገና ዐይኖቼን ከማንጠግቦሽ ላይ ሳላነሣ ።

“ እም ! ደሞ መፈላሰፍ ጀመርክ ። እስኪ ምስኪኗን ለቀቅ አርጋትና ሌላ ጨዋታ አምጣ ” አለችኝ ፣ አፏን ጠመም አርጋ እያሸሟጠጠች ።

ለሙዚቃ ከፍተኛ ግምት ይኑረኝ እንጂ ፣ በመጠጥ ቤት ሁካታ መኻል ለሚሰማው ያዝማሪ ዜማ እንኳ ደንታ አልነበረኝም ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ማንጠግቦሽንና ዜማዋን ፣ ውባለንና መሰንቆውን አለቅጥ መውደድ ጀምሬያለሁ ። ወደዚሁ ቡና ቤት እንዳዘወትር የሳቡኝ እነርሱዉ ናቸው ። የማንጠግቦሽን ጣዕመ ዜማና ልብ የሚነኩ ግጥሞች ለማዳመጥ ስመላለስ ነው መሰለችን ጓደኛ ያደረግሁት ። አንዳንድ ቀን ቀስ በቀስ እየተላመድሁትና እየወደድሁት የመጣሁት ፣ ‘ ይህ ሁኔታ የመጠጥ ሱሰኛ ያደርገኝ ይሆን ? ’ እያልኩ ሥጋት ላይ ልውደቅ እንጂ መመላለሱን ግን አጥብቄዋለሁ ። ከመሰለች ጋርም ወዳጅነትን መሥርቻለሁ ። እንዲያውም ሰሞኑን ኦና ቤቴ እያስጠላኝ በመምጣቱ ፣ እዚያው መጠጥ ቤት አምሽቼ ከመሰለች

ጋር ሌሊቱንም ማሳለፍ አዘውትሬያለሁ ። የተወዳጇኋት ሴትኛ አዳሪዋ መሰለች ፣ የምደጋግመው አልኮል ፡ የመጠጥ ቤቱ ሁካታና ጨዋታ ፣ የውባለ መሰንቆ ለደንበኝነቴ ድጋፍ ሰጪ ይሁኑ እንጂ ፣ ልቤን የማረኩትና የሚያመላልሱኝ ግን ማን ጠግቦሽ ፣ አሳዛኝ ፊቷ ፣ ለዛ ያለው ዜማዋ ፣ የድምፅዋ ቅላጼና የምታኝጎራጉዳቸው ግጥሞች ናቸው ፣ በቁጥጥር ሥር ያዋሉኝ ። መላ ሁኔታዋ በሠራ አካላቴ ልዩ ስሜትን አሳድሮብኛል ። ቀና ብዬ አየሁዋት ።

“ ዕንቁላል ሲያዩት ይላል ዋጡኝ ዋጡኝ
ከርስዋ ጋር ስጫወት ሌሎች አመለጡኝ ። ”

አንድ ሰው ብር ሳይከፍላት ብዙ ያቆያት እንደሆነ የምታዜመው ግጥም ነው ። እፊት ለፊቷ ቆሞ ግጥም ይነግራት የነበረው ሰው ከት ብሎ ሣቀና አንድ ባለ አምስት ብር አውጥቶ ግንባሯ ላይ ለጠፈላት ። በግጥምና በዜማ አመስግና ወደ ሌላ አዲስ ሰው ፊቷን መለሰች ።

“ እረ እየው ድማሙ . . .
ትጉህ ሠራተኛ ደከምኩ እማይለው
ፒያሳ ፣ መርካቶ ፡ ካዛንቺስ ሳይቀረው

አብዱ ራህመቶ፣ «ዕኩይ አጋጣሚና አንባቢው»፣ <u>እነሆ አጫጭር ልቦለዶች</u>፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ **1980**።

– የአዝማሪዋ ህይወት ምን እንደሚመስል አብራራ።

– በልብወለዱ ደራሲዋ በአንባቢው አመለካከት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የተጠቀመችባቸው ቴክኒኮች ላይ አስተያየት ስጥ።

– የአጭር ልቦለዱ መቼት ገፀባህሪያቱን በማሳየት ረገድ ያለውን አስተዋፅኦ ግለፅ።

– ስለጽሁፉ ያለህ አጠቃላይ አስተያየት ምንድነው?